# “ቦ ግዜ ለኩሉ”!

መነሻዬም ሆነ መድረሻዬ ሰሞነኛውን በጋዜጠኞች መሃል የሚንከባለለው ጉዳይ ነው። ይሁነኝ ተብሎ ይሁን ድንገት የተለኮሰው እሳት ይነዳል፤ ሲዳፈን ቆይቷልና እነሆ ግዜውን ጠብቆ መጣ። ጠቢቡ ሰለሞን እንዳለው “ቦ ግዜ ለኩሉ”።

<u>እስኪ እንደመነሻ፦</u> አመታትን ተሻገረው የጋዜጠኞች የመገናኛና የመወያያ ኢሜል ፎረም ውስጥ ከሶስት ሳምንት በፊት በዳዊት ከበደ በኩል የተሰራጨውና በኋላም አጥጋቢ ባልሆነ ምክንያት እንዲነሳ የተደረገውን የአቶ ከፋለ ማሞን ከኢሳት የሰራ መልቀቂያ ደብዳቤና ጥቂት ምልልሶችን አንብቤ በተለመደው የትዝብት ዝምታዬ ላልፈው ወስኜ ነበር። ተከትሎም በተነሳው አቶ ከፋለ ማሞ ከሥራው ከተባረረ በኋላ ሰላሰራጨው “የሥራ መልቀቂያ”፤ የኢሳት አለቃው ፋሲል የኔአለም ስለሰነዘረው የመከላለያ ሃሳብ ወይም ዳዊት ከበደ “ነጻ ሚዲያ በሚል የተጀመረው ኢሳት እንዴት ግንቦት ሰባት መዳፍ ላይ ወደቀ?” ሲል ላነሳው ሃሳብ አልተገረምኩምም ነበር። በአንድ በኩል ይሄ አፈትልኮ የወጣው ደብዳቤ ጭብጥ ስጋት ያሳደረባቸው ጉዳዩን ሊያዳፍኑ መድከማቸውን ፤ በሌላው ደግሞ ስለጉዳዩ በቂ እውቀት ጨብጠ ዘላቂ መፍትሄ ለመሻት በቅን ልቦና የሚጥሩ መኖራቸውን ስመለከት ዝምታዬን እሰብር ዘንድ ግድ አለኝ።

በዚህ ጉዳይ ላይ በቅድሚያ አንድ ነገር ማንሳት እወዳለሁ። በወቀቱ ማድረግ ያለብኝን ሁሉ ከፈጸምኩ በኋላ ሰሚ በመጥፋቱና  የዘመኑ የዲያስፖራ የፌና ፖለቲካና ጩኸት አቅሜን በመፈታተኑ ጊዜ አስኪፈታው በይደር ፋይሌን አስሬ አኑሬው ነበር። ግዜ የጣለውን ግዜ ያንሳው በሚል። የጉዳዩ ፋይዳና አሳሳቢነትም በቅርቡ ወደ ስደት ዓለም ከተቀላቀላችሁን ጥቂት ባልደረቦቼ በስተቀር የተፈጸመውን ደባ ለምናውቀው የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞችና የውጭ ታዛቢዎች የጎላ ነው። ምናልባትም “በኢትዮጵያችን እንዲሰርጽ እየታገልን ነው” ለምንለው ሃሳብን የመግለጽ  ነጻነት፤ የህግ የበላይነት ለውጥ ድክመታችንን በግልጽ የምንመለከትበት መልካም አጋጣሚ እንደሚሆን አምናለሁ።

ይኸው ለሁሉም ግዜ አለው እንደተባለው አቶ ከፋለ ማሞ ብዙም ሳይቆይ አውቆትም ይሁን ሳያውቀው በሁለት/ሶስት አመት እድሜው *“ከሰራ ተባረርኩ”* ባለበት ደብዳቤው ውስጥ እውነትን ይዞ ከተፍ አለ። ለካንስ አበው “ነግ በኔ” የሚሉት ለዋዛ አልነበረም። “ጊዜ”ን እድሜ ይስጠው!

ወደ ነጥቤ ልግባ፤ ለአስረጂነት እንዲያግዘኝ ጠቃሚ ያልኩትን ሃሳብ እያካፍልኩ እዘልቃለሁ።

<u>በኔዘርላንድስ ስለምንገኝ የኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞች፦</u> በኢትዮጵያ የጋዜጠኝነት ሙያቸው ሳብያ ከደረሰባቸውን ተደጋጋሚ እስራት፤ የገንዘብ ቅጣት፤ ወከባ በመሸሽ በተለያዩ አጋጣሚዎች መኖሪያቸውን በስደት ኔዘርላንድስ ያደረጉ ጋዜጠኞች ቁጥር ከአስር አያንስም። ነፍሱን ይማረውና በሞት የተለየንን ጋዜጠኛ ተፈራ አስማረን፣ በቅርቡ የተቀላቀሉን፤ ሆላንድን ትተው ወደ ሌላ አገር የሄዱትንና ድምጻችውን አጥፍተው በሌላ ስራ ላይ የተሰማሩትን ጨምሮ ማለቴ ነው።

<u>ስለ ነጻ አማራጭ የመገናኛ ብዙሃን ማቋቋም፦</u>- በተለይ በነጻው ፕሬስ ላይ በኢትዮጵያ ስንንቀሳቀስ ከነበርነውና በዘጠናዎቹ አጋማሽ ላይ ለስደት ከተዳረግነው ጋዜጠኞች መካከል ጥቂቶቻችን በሙያችን መቀጠልና እራሳችንንም ሆነ አገራችንን መጥቀም የምንችልበትን አማራጭ መንገድ ማፈላለግ የተያያዝነው ከጅምሩ ነበር። ይህንንም ለማሳካት በኢትዮጵያ ኮምዩኒቲ የስነጽሁፍ ኮሚቴ፣ የቀስተ-ዳመና ሬዲዮ፤ ኢትዮጲስ በስደት ጋዜጣ እና በኢትዮ-ቲቪ-አምስተርዳም ስም የተደረገውን ሙከራና ጥረት መጥቀስ ይቻላል። በነዚህ መድረኮቸ ላይ በተናጥል ወይም በቡድን እንደየአመለካከታችንና ፍላጎታችንም ተሰማርተናል።

ነገር ግን ሁላችንንም በጋራ ሊያሳትፈን፡ የቻለው የኢትዮ-ቲቪ ሳምንታዊ የቴሌቭዥን አግልግሎት ብቻ እንደነበር ለመግለጽ እወዳለሁ። **ለምን?** አንደኛ፦ ኢትዮ-ቲቪ ከጅርባው፣ ከፊቱም ይሁን ከጎኑ ማንም የባለቤትነት ወይም የሽርክና መብት ጥያቄ የሚያነሳበት አልነበረም፤ ሁለተኛ፦ እንደ እሳት የሚያፋጅ የጥቅም ጭቅጭቅ አልነበረበትም። **ምክንያቱም** የሚያጣላ የመዋጮም ሆነ የድጎማ ገንዘብ ስላልነበረ ነው!

ይህ ሙያዊ ፍቅር የተሞላበት የቴሌቭዥን ሥርጭት የኢሳት ሳተላይት ቴሌቭዥን በይፋ እስከጀመረበት ዋዜማ ለአስር አመታት አገልግሎት ሲሰጥ እንደቆየ በኔዘርላንድ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን እማኞች ናቸው። ለኢትዮ-ቲቪ የዋለውን የአንዳንዶቻችንን ጊዜ፣ ጉልበት፣ ገንዘብ፣ እውቀትና የግል ንብረት መሰዋትነት አንድ ቀን ታሪክ ይፋ ያደርገዋል።

በዚህ መልክ ከአስር አመት በላይ የዘለቀው የኢትዮ ቲቪ ሥርጭት አገልግሎቱን ማስፋፋትና በተለይ በስደት ላይ የሚገኙ የሙያ ባልደረቦቼ የሚሳተፉበት መድረክ እንዲሆን ጽኑ ፍላጎትና አላማ ቢኖርም አቅም የሁል ጊዜ ፈተና ነበር። ከማንኛውም የ3ኛ ሃይል ተጽእኖ ነጻነታችንን እንዳስጠበቅን ለዚህ ችግር ዘላቂ መፍትሄ ማፈላለግ በጀመርንበት ወቅት (ከ2004-2006) የነበረን የጋራ ተነሳሽነትና ጥረት ጤነኛ ነበር። ይሁንና ባልደረባቸን ክንፉ አሰፋ ከ2005 - 2006 ዓ.ም፤ በኢትዮ-ቲቪ አገልግሎትም ሆነ በፋውንዴሽኑ ሥራ ላይ አብሮን አልነበረም።

<u>**የኢትዮ-ዳች ጋዜጠኞች ዓለም አቀፍ ጉባኤ፡**</u> ከ2005 - 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ አንድ ዓለም አቀፍ የነጻው ፕሬስ ጉባኤ የማድረግ ሃሳብ ተጸንሶ መተግበር የተጀመረበት ወቅት ነበር። የጉባኤውን አስፈላጊነትን ከግምት በማስገባት ተነሳሽነት የወሰድነው እኔ እና አቶ ከፋለ ከኢነጋማ ፕሬዚዳንት ክፍሌ ሙላትና በስደት ላይ ከሚገኙ የኢነጋማ  አባላት ጋር በመመካከር ነበር።

አይነተኛ አላማውም አገለግሎቱ በኔዘርላንድስ በተለይም በአምስተርዳም የተገደበው ሳምንታዊው ኢትዮ-ቲቪ የአገልግሎት ሥርጭቱ እንዲስፋፋና በተለይም በስደት ላይ የሚገኙት የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች በዋናነት የሚሳተፉበት እንዲሆን ነበር። ይህ ዓለምአቀፍ ጉባዔም ከማንኛውም የፖለቲካም ሆነ የቤተ እምነት ተቋም ተጽእኖ ነጻ የሆነ አማራጭ የሬዲዮና ቴሌቪዠን ጣቢያ ለማቋቋም ወደተግባራዊ ርምጃ የሚያሸጋግር ምክክር ለማድረግ የታለመ ነበር። የአጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ በወቅቱ በኢትዮጵያ በ1997 ዓ.ም ከተካሄደው ምርጫ ጋር በተያያዘ በተወሰደ የሃይል ርምጃ ነጻው ፕሬስ እጅግ ለከፋ አደጋ ተጋለጠ። የአማራጭ ሚዲያ አስፈላጊነትም በእርግጥም አስፈላጊነቱ በሁሉም ዘንድ ጎልቶ ወጣ። በዚህም ለኢትዮጵያ ህዝብ አማራጭ የመረጃ ምንጭ ሆነን እናገለግላለን የሚል ብርቱ እምነት ነበረን።

ክንፉ አሰፋ ይህ ጉባኤ ከመደረጉ ጥቂት ወራት በፊት የጉባኤው አዘጋጆቸን መልሶ ተቀላቅሎ እስከ ጉባኤው ማግስት በህዝብ ግንኙነት የሥራ ድርሻ አገልግሏል። ይሁንና የዚህን ስራ ሃላፊነት ከወሰደው ድርጅትም Foundation for Ethiopian Information and Documentation in the Netherlands, FEIDIN ሆነ ከኢትዮ-ቲቪ አገልግሎት ጋር የነበረው ግንኙነት እንደተቋረጠ ነበር።

ይህንኑ ተከትሎ የዓለምአቀፍና የኔዘርላንድስ የሙያ ባልደረቦቻችንንና አጋሮቻችንን ትብብር በመጠቀም የኢትዮ-ዳች ጋዜጠኞች ዓለም አቀፍ ጉባኤን በጁን 2006ዓ.ም ለማከናወን በቃን። በዚህ ጉባኤ ላይ ሆላንድ ውስጥ በስደት ላይ ከምንገኘው የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች በተጨማሪ በርካታ ኢትዮጰያዊያን ነዋሪዎች፣ የህዝባዊ ድርጅቶች ተወካዮችና የኔዘርላንድስ የሙያ አጋሮቻችን ተገኝተዋል። በተጨማሪ የኢነጋማ ፕሬዜዳንት ክፍሌ ሙላትንና በወቅቱ የአንጋፋው የኢትዮጰያ መምህራን ማህበር ፕሬዜዳንት የነበሩት ዶ/ር ታዮ ወልደሰማያትን በዋና አወያይነት ተገኝተዋል። እንዲሁም መቀመጫቸውን በአፍሪካ፣ አውሮፓና አሜሪካን አገር ያደረጉ አስራ አምስት የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞችና አጋሮቻቸው ለሶስት ቀን ለመሰባሰብና ለመምከር ችለን ነበር።

በጉባኤው ማብቂያ ላይ ከላይ የተተለመውን ግብ ለመምታት አቶ ከፋለ ማሞ፣ ክንፉ አሰፋ፣ ሶስት የዳች የሙያ አጋሮቻችን፣ ዶ/ር ወንድሙ መኮንን፣ አቶ አበራ ለማን እና እኔን ያካተተ የመፍትሄ አፈላላጊ (Task force) ተቋቋመ። ጉባኤው በተጨማሪም ዶ/ር ታዬ ወልደሰማያትን፣ ክፍሌ ሙላት፣ ኤሊያስ ወንድሙ፣ ዶ/ር ሼክስፒር ፈይሳን እና የIFJ ተወካዩን ገብርኤል ባግሎን ያካተተ የመማክርት ኮሚቴ ሰይሞ ነበር የተጠናቀቀው።

<u>**ነጋሪት ሬድዮ ፕሮጀክት ምስረታ፡**</u> የመፍትሄ አፈላላጊ(Task force) ኮሚቴ ስራውን በሰባት ወራት ውስጥ ሲያጠናቅቅ Foundation for Independent Media for Ethiopian (FIME) በሚል አዲስ አደረጃጀት የመጀመሪያውን የቦርድ አባላት ሰይሟል። በዚህም መሰረት አቶ አበራ ለማ፣ ዶ/ር ወንድሙ መኮንን አቶ ከፋለ ማሞ፣ አቶ ሙሉጌታ ገብሬና ሁለት የዳች የሙያ ባልደረቦቻቸን በቦርድ አባልነት ተካተዋል።

ከ2006 ዓ.ም ዓለምአቀፉ ጉባኤ ጥንስስ አንስቶ የኔ የሥራ ድርሻ የታስክ ፎረሱንና የቦርዱን ሥራ በፕሮጀክት አስተባባሪነት ማሳካት ነበር። በስራ ሂደቱ ብዙ ትምህርት አግኝቼበታለሁ፤ ሰፊ ጥናትና ውይይቶቸን እያደረግኩ የነጋሪት ሬዲዮና ቴሌቪዥን ፕሮጀክት ፕርፖዛልን አርቅቄአለሁ። አቶ ከፋለ ማሞ፣ ዶ/ር ወንድሙ መኮንን፣ አቶ አበራ ለማ አስፈላጊውን እርማትና ማሻሻያ በማድረግና ሰነዱን በማጎልበት ብርቅ ጊዜአቸውን እውቀታቸውን በቅንነት በማበርከታቸው የመልካም ውጤት ባለቤት ልንሆን ችለናል።

የPRESS NOW ድርጅት በዳይሬክተሩ አማካኝነት ከ2006ቱ ዓለምአቀፍ ኮንፍረንስ አንስቶ የታስክ ፎርሱን ሥራ በማመቻቸት፤ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሉን በማጠናከር፣ ለሥራው ለተዘጋጁ ጋዜጠኞችና በጎፍቃደኞች ስልጠናና አስፈላጊውን የሥራ ግንኙነት በማመቻቸት ፕሮጀክቱን ለማሳካት ያበረከተው አስተዋጽኦ የላቀ እንደነበር ሳይጠቀስ አይታለፍም። በተለይ አቶ አበራ ለማ እና ዶ/ር ወንድሙ መኮንን በታስክ ፎረስ በኋላም የቦርድ አባልነት ሃላፊነታቸው ሳብያ ሥራቸውንና ቤተሰቦቻቸውን እየተዉ ከኖርዌይና ከእንግሊዝ እየተመላለሱ ላበረከቱት ግልጋሎት ልዩ አክብሮት ይገባቸዋል።

አቶ ከፋለ ለኢሳት ቢሮው መልቀቂያ ብሎ በጻፈው ደበዳቤ ላይ *“የማስታወቂያ ቢሮ መኮንኑ ክንፉ አሰፋ ....አግባብነት ያለው ሃላፊነት በክንፉ አሰፋ አማካኝነት ሲካሄድ የቆየና...”* እያለ ያንቀለጳጰሰበትን ምክንያት ብረዳውም፤ ዳዊት ከበደ በተደጋጋሚ *“የአማራጭ መገናኛ ብዙሃን ለማፈላለግ ውክልና የተሰጠው ክንፉ አሰፋ ነው”* የሚል ሃሳብ ከየት አምጥቶት እንደሚያንከባልለው መረዳት ይቸግረኛል። ክንፉ አሰፋ የነጋሪት ሬዲዮና ቴሌብዥን ፕሮጀክት ፕሮፖዛልን በኢሜል አድራሻው እስከላኩለት ድረስ ለብዙ ሥራዎቹ እንግዳና ተሳትፎው በርቀት ነበር። የኢትዮ ቲቪ፣ FEDINንም ሆነ የFIME አባል አልነበረምና።

የክሬዲት ሽሚያ ካልሆነበት በስተቀር “የኢነጋማ ዓለምአቀፍ ኮሚቴ”ም በኢትዮ-ቲቪ፣ የ2006ዓ.ም ጉባኤም ሆነ የነጋሪት ሬዲዮና ቴሌብዥን ፕሮጀክት ላይ የሚሽልልበት ተግባር አልፈጸመም። በእርግጥ ሃገር ውስጥ በነበርንበት ወቅት በኢነጋማ ምሥረታና የማህበሩን ስራ ለማካሄድ ያደረግነው ጥረት እንደ አንድ ምዕራፍ ይታወሳል። እዚህ ሆላንድ ለተፈጸመው ተግባር ግን፦ እኛ እንደ ጋዜጠኛ፤ FEIDIN በኋላም FIME እንደ ድርጅት ነን ተወቃሽም ሆነ ተወዳሽ የምንሆነው። ለነገሩስ ኢነጋማ ዓለምአቀፍ ኮሚቴ የተባለው ተቋም ተሞከረ እንጂ አለ እንዴ? እንግዲህ እኔም፣ አቶ ከፋለም፣ ክንፉም በህይወት አለን፤ በመግቢያዮ በኔዘርላንድ ከአስር በላይ ኢትዮጵያዊያን ጋዜጠኞች ይኖራሉ ያልኳቸውን እንኳ ማሰባሰብ ያልተቻለው ኢነጋማ-አኮ? ሌላው ቀርቶ እንደ ድርጅት እንኳ መቼና የት ተመዝግቦ ነው? ነው ወይስ ዛሬም በጨበጣ? ለምን ጋዜጠኛውን እንደምናደናግር አይገባኝም። ከእንግዲህ ግን መልስ የሚሻ ጥያቄ ይመስለኛል።

ወደ ነጥቤ ልመለስ ፤ የእርዳታ ማሰባሰብ ዘመቻ!

የነጋሪት ሬዲዮና ቴሌብዥን ፕሮጀክት አመታዊ በጀት ስሌቱ 285.000 ኤሮ ነበር። የፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ እንደተጠናቀቀ በኢሜል፣ በደብዳቤና በግንባር በማቅረብ የእርዳታ አድራጊዎችን ደጅ ጥናት ተጀመረ። እዚሁ ሆላንድ፣ ኖርዌይ፣ ጀርመን፣ ፊንላንድና የአውሮፓ ህብረት ተሰፋ የተጣለባቸው በጎ አድራጊ ድርጅቶች ነበሩ። በዚሁ መሠረት ከአቶ ከፋለና እና ሌሎች የቦርድ አባላት ጋር በመወያየት ለኖርዌይ አቶ አበራ ለማ፤ ለአውሮፓ ህብረት ክንፉ አሰፋ፤ ሆላንድን ጨምሮ ለተቀሩት አገራት ድርጅቶች እኔ እንድንከታተል ተስማማን።

በዚሁ መሰረት ለኖርዌዩ የበጎአድራጎት ድርጅት በኢሜል የገንዘብ እርዳታ ጥያቄ ሳቀርብ ለቀጣይ ክትትል ከአቶ አበራ ለማ ጋር ግንኙነት እንዲያደርጉ አድርጌአለሁ። ከአውሮፓ ህብረት ጋር ማድረግ ለነበረብን ግንኙነት ክንፉ አሰፋ “ቀጥታ ግንኙነት አለኝ” በማለቱ፤ በአቶ ከፋለ ማሳሰቢያም ጭምር ሙሉ ሃላፊነቱን እንዲወስድ በተስማማን ማግስት ነበር የነጋሪትን ፕሮጀክት ፕሮፖዛል በቀጥታ በኢሜል የላኩለት።

ስድስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከሆላንድና ከጀርመን ከሶስት ድርጅቶት ብቻ የ110.00 ኤሮ ቃል የጽሁፍና የቃል ዋስትና (grant) አገኘን። እዚሁ ሆላንድ ውስጥ እኔና ከቦርድ አባላት መካከል አቶ አበራ ለማ ከአንድ የበጎ አድራጊ ከድርጅ ባለስልጣኖች ጋር ባደረግነው ውይይት ፕሮፖዛላችንን በአንዳንድ ነጥቦች ላይ ካሻሻልን እስከ 65.00 ለሶስት አመት በተከታታይ ሊሰጥ እንደሚችል ተስፋ ሰጠን። ብናደርገው ኖሮ 176.000 ኤሮ ነበር ማለት ነው።

በሌላ በኩል ከኖርዌይና ፊንላንድ ተሰፋ የሌለው ዜና ደረሰን። ደጃቸውን ያንኳኳንባቸው ድርጅቶች በየራሳቸው ምክንያት በወቅቱ ሊረዱን እንደማይችሉ ገለጹልን። የአውሮፓ ህብረት ጉዳይ ግን ለረጅም ጊዜ *"ተሰፋ አለን፤ ፕሮሰስ ላይ ነው"* ከሚለው የክንፋ አሰፋ መልስ ውጭ የተጨበጠ ውጤት አልነበረም።

<u>ስለ ነጋሪት ሬድዮ ፕሮጀክት መስተጓጎል፦</u> ይህ በእንዲህ እንዳለ አዲስ ጤነኛ ያልሆነ ሁኔታ መከሰት ጀመረ። እዚህጋ ወደኋላ መለስ አድርጌ ጥቂት ላስረዳ። ለስምንት አመታት የኢትዮ-ቲቪን አገልግሎት ስንሰጥ እንደ እሳት የሚያፋጀን ጉዳይ አልነበረም፤ ምክንያቱም ገንዘብና ጥቅማጥቅም አልነበረበትምና ነው? በተጨማሪም ኢትዮ-ቲቪ የነጻ አገልግሎት ስለነበር የሃላፊነት ግዴታም፤ ጥያቄም፤ ተጠያቂም አልነበረም። አንድ ሰው ሲመቸው ያገለግላል፤ ሳይመቸው ይቀራል።

የነጋሪት ፕሮጀክት ግን ሙያዊ ክህሎትንና በተገቢው የሥራ መደብ ተገቢውን ባለሙያ መመደብ ይጠይቅ ነበር። ማንም በእድሜው፤ በዝናው፤ በኩርፊያው ወይም አመሉን በመስጋት የማይገባውን ሃላፊነት ወስዶ ሥራውን በጉልበት ወይም በእንዝላልነት ማካሄድ አይችልምና። የነጋሪት ፕሮጀክት ትርፋማ ያልሆነ፤ ወይም የንግድ ድርጅት ስላልሆነ በቦርድ እንዲተዳደር የግድ ነበር። ይህን አሰራር መልመድ እንዳለብንና ሁላችንም እንደየፍላጎታችን፤ አቅማችንና ጊዜያችን በሥራ ላይ እንድንሰማራና እንደየአገልግሎታችን እንድንከፈል የቦርዱ አቋም ነበር።

ምክንያቱም በዚህ ሃገር ህግ መሰረት አንድ ሰው የቦርድ አባል ከሆነ በተደራቢነት የአገልግሎቱም ሠራተኛ ሆኖ ደሞዝ ተከፋይ መሆን አይችልም። በግልጽ ለመናገር፤ አንዳንዶቻችን የግልና የጋራ ሙያዊ ተጠያቂነት ላለበት አሰራር ዘዴ ዝግጁ አልነበርንም።

በአቶ ከፋለ በኩል *"ከዚህ በፊትም የምንሠራው በጋራ ነው፤ አሁንም ሥራውን በጋራ ሠርተን የሚገኘውን ገቢ በጋራ እየተካፈልን፤ ለሌቹም እንደአግባብነቱ የሚደርሳቸው ይደርሳቸዋል"* የሚል ፍጹም የሚጻረር አቋም ጸና። አቶ ከፋለ ከቦርዱና በሥራው ላይ ሊሰማሩ በዝግጅት ላይ ከነበሩት ጋዜጠኞችና በጎአድራጊዎች በተለየ ሁኔታ "ኮር ግሩፕ" የሚለው ነበር። ይህ "ኮር ግሩፕ" ቀደም ሲል የኢትዮ ቲቪ ሳምንታዊ አገልግሎት ላይ ከፊት ተሰልፈው ከነበሩ በጎ ፍቃደኞች መካከል እራሱን፣ ክንፋን፤ አፈወርቅንና እኔን የሚያካትት ነበር። ይሁንና ከFIME ቦርድ ምሥረታ በኋላ የፈረሰና ከአሰራር ደንብ ውጭ በመሆኑ ከአቶ ከፋለ በስተቀር የቦርዱ አባላት ይቃወሙ ነበር። ይህም የኔም እምነት ነበር።

በዚህ ሂደት ውስጥ "ኮር ግሩፕ" ተብለን በተሰየምነው ግለሰቦች መካከል እጅግ በርካታ የሚባል የግልጽ ውይይት፤ ክርክርና ሽምግልናዎችን አድርገናል። የሁሉም ሙከራ ውጤት ግን ከዜሮ በታች ነበር። ከዚህ አይነት አሰራር መውጣትና ሃላፊነትን እንደ ልካችን መውሰድና በአግባቡ የመወጣት አቅም ሲሳነን ወደ ስብቀት፣ መቀናናት፣ ኩርፊያና ስም ማጥፋት ዘለቅን። የጭቅጭቅ ጅማሮአችንና የሚፈጸሙው የሸፍጥ አካሄድ ያላማረውና በገንዘብ ያዥነት ያገለግል የነበረው የቦርድ አባል ሙሉጌታ ገብሬ በዚህ ጊዜ ነበር ሃላፊነቱን በጽሁፍ ያነሳው። የሙሉጌታን ውሳኔ ተከትሎ በተጠራው የቦርድ ስብሰባ ላይ በአቶ ከፋለ አቅራቢነት ክንፋ አሰፋ የFIME በቦርድን ተቀላቀለ።

<u>የነጋሪት ፕሮጀክት መሰረቅ፦</u> ከላይ እንደጠቀስኩት በሆላንድና በጀርመን ከሚገኙ ሶስት ድርጅቶች በጠቅላላ ድምሩ 111.000 ኤሮ በጽሁፍና በቃል የተረጋገጠ የእርዳታ ስምምነት ነበር። በተጨማሪም ከአራተኛው ድርጅት የተሰጠን በየአመቱ የ65.000 ኤሮ ተሰፋ ነበር። የአውሮፓ ህብረት ጉዳይ ግን ከተድበሰበሰው የክንፋ መልስ ውጭ የተጨበጠ ነገር አልነበረም። ሁኔታውን ከግምት በማስገባት በቦርዱ ውሳኔ ተጨማሪ ክትትል እንዳደርግ ሆነ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አቶ ከፋለ፣ ክንፋ፣ አፈወርቅና እኔ በተገኘንበት አንድ ውይይት ላይ ክንፋ አሰፋን "የነጋሪት ፕሮጅክት ፕሮፖዛሉን ለአውሮፓ ህብረት ካቀረብክ ያቀረብክበትን መረጃ ስጠን። የፕሮጅክት መሪ ስለሆንኩም ማወቅ ይገባኛል፤ አስፈላጊ ከሆነም ብራሰልስ አብረን ልንሄድ እችላለን" ስል ቀጥተኛ ጥያቄ አቀረብኩለት። ከረጅም ክርክር በኋላ ቤልጀየም አውሮፓ ህብረት ጽህፈት ቤት አብረን ልንሄድ ተስማምተን ተለያየን።

ከሁለት ቀን በኋላ በድጋሚ በኢትዮጵያ ማህበር ጽህፈት ቤት ውስጥ ባደረግነው ስብሰባ ግን ክንፉ “አዲስ ሃሳብ” ይዞ ቀረበ። በርግጥ ከእርሱ እስኪመጣ መጠበቅ ስለወሰንኩ እንጂ ሃሳቡ ለእኔ አዲስ አልነበረም። በግሌም መረጃዎችን ማሰባሰብ ጀምሬ ነበር። በዚያው ሰሞን አንዳንድ የድህረገጽ ዜና ምንጮች የነጋሪት ፕሮጀክት ስለመጠለፉ ፍንጭ መስጠት ጀምረው ነበር።

በዚያ ውይይት ላይ በመጀመሪያ ነዋሪነቱ ቤልጅየም በሆነው አቶ አበበ ቦጋለ አማካኝነት በኋላም ነዋሪነቱ ሆላንድ ከሆነው መስፍን አማን ጋር ክትትል ያደርግ እንደነበር አስረዳ። ክንፉ በተጨማሪም በወቅቱ በአውሮፓ የሥራ ጉብኝት ያደርግ ከነበረው የቅንጅት ልዑክ ቡድን አባላት መካከል ከአቶ ሙሉነህ እዮኤል ጋር የአውሮፓ ህብረት ጽህፈት ቤት ውይይቶችን እንዳደረገና የአውሮፓ ህብረትም ከቅንጅት ጋር አብረን ከሰራን የገንዘብ እርዳታ እንደሚያደርግልን ቃል መግባቱን ይገልሳል። ይህንን ጉዳይ አቶ ከፋለም ከአቶ ሙሉነህ ጋር መወያየቱንና መስማማታቸውንም ያረጋግጥልኛል።

ቅንጅት አንደኛ የፖለቲካ ድርጅት በመሆኑ ሁለተኛ በአውሮፓ ህጋዊ ህልውና ስለሌለው ከእኛ ጋር መስራቱ ለእኛም ለቅንጅትም የተሻለ አማራጭ ነው ሲሉ ሊያሳምኑኝ ሞከሩ። በዚህ ነጥብ ላይ እንደማንስማማና የመነሻ ሃሳባችንም እንዳልሆነ አቋም ይዤ ሙግት መግጠም ጀመርኩ። የአውሮፓ ህብረት የነጋሪት ፕሮጀክትን ለመርዳት *“ከቅንጅት ጋር መሻረክ አለባችሁ”* የሚል ትእዛዝ ሊያስተላልፍ አይችልም፤ ቢፈልግ ቅንጅትን አሊያም የኛን ፕሮጀክት ሊያግዝ ይችላል፤ የሚል ጽኑ አቋም ያዝኩ። ከዚያች ቀን አንስቶ አቶ ከፋለ እና ክንፉ በአንድ በኩል እኔ በሌላ መስመር ላይ መቆማችንን በግልጽ አረጋገጥን።

የሚቀጥለው እርምጃዬ ይህንን አቋማቸውን ለጠቅላላ ቦርድ አባላት አስረድቼ አጠቃላይ ጉባኤ መጥራትና ማመቻቸት ነበር። ይህንንም በአጭር ጊዜ ውስጥ አደረኩት። በስብሰባውም ላይ በሆላንድ ነዋሪ የሆኑና በሽምግልና አብረውን ሲወጡ ሲወርዱ የነበሩትንና የፕሮጀክቱ ተባባሪነት የነበሩት የPress Now ዳይሬክተር Wilco de Jong በታዛቢነት ተገኙ። አቶ ከፋለም ሆነ ክንፉ የቦርድ አባላትን የሚያሳምኑበት አንድም ነጥብ አልነበራቸውም። በዚህ ምሽት የነበረውን የአቶ ከፋለና ክንፉን አቀራረብና አገላለጽ አሳፋሪ ከማለት በስተቀር ሌላ አስተያየት የለኝም። ከታዛቢዎች መካከል በእነርሱ በኩል ተመርጠ ውይይታችን ላይ የተገኘውና የታዛቢዎችን ሪፖርት እንዲያቀርብ ሃላፊነት የተሰጠውን የአቶ ቦጋለ ካሳዬ ሪፖርት በአባሪነት አያይዤዋለሁና እናንተው ተመልክታችሁ ፍርዱን ስጡ።

ሳይውል ሳያድር የክንፉ አሰፋ ሴራ ከነመረጃው ከእጄ ላይ ወደቀ። በቅድሚያ ከእኔም ሆነ ቦርዱ እውቅና ውጪ የሚፈልጋቸውን ግለሰቦች በማሰባሰብ በመኖሪያ ቤቱ አድራሻ አዲስ ድርጅት አቋቋመ። ቀጥሎ በFIME የቦርድ አባልነቱ ምክንያት በእጁ የገባውን የነጋሪት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል የስም ለውጥ ብቻ በማድረግ ሌላ ተመሰሳሳይ የሬዲዮ ወይም ቴሌቭዥን ተቋም ሲያቋቁም ተጋለጠ። ይኸው አሰመስሎ ያዘጋጀውን ፕሮጀክት ፕሮፖዛልና ለአውሮፓ ህብረት የ2.5 ሚሊዮን ኤሮ የእርዳታ ያቀረበበት ሰነድ ከእጃችን ገብቷል። ይህ ሰነድ ይዘቱም ቅርጹም የነጋሪት ፕሮጅክት ካርቦን ኮፒ ነበር።

በዚህ ጉዳይ ላይ በድጋሚ በአስቸኳይ የተሰበሰበው ቦርድ ክንፉ አሰፋ ስለፈጸመው ድርጊት ማብራሪያ እንዲሰጥ ቢጠይቀውም *“ያመንኩበትንና የፈለግኩትን የማድረግ መብቴ የተጠበቀ ነው”* ከማለት ውጭ የማምለጫ መንገድ አልነበረውም። የሚገርመው የቦርዱ ሊቀመንበር አቶ ከፋለ እንዲህ ዛሬ በኢሳት መሰናበቻ ደብዳቤው *“ከበላይ አካል ተወዳጅነትን ለማትረፍ ሲባል የፓርቲ ፖለቲካን የማስቀደም አባዜ አዝማሚያ ከእለት ወደእለት እያየለ መምጣት.....”* የሚል እሮሮ ማሰማቱ ላይቀር *“መብቱ ነው”* በማለት ስለድርጅቱ ሰነድ መሰረቅ ማንሳትም መወያየትም አልፈለገም። ክንፉ ግን ስለፈጸመው ተግባር ህግ ፊት እንደሚያስቀርበውና እንደሚያስጠይቀው ጠንቅቆ ስላወቀ ከመለሳለስ ውጭ የወሰደው እርምጃ አልነበረም። በስተመጨረሻም ከአቶ ከፋለ በስተቀር በሙሉ ድምጽ ክንፉ አሰፋ ከቦርድ አባልነቱ እንዲሰናበትና የሚመለከታቸው ክፍሎች በሙሉ ጉዳዩን እንዲያውቁት ይወሰናል። ክንፉም ሁኔታው ወደ ህግ ከተመራ የሚገጥመውን ችግር በመረዳት ውሳኔው የማርያም መንገድ ስለከፈተለት በምስጋና የዚያኑ እለት ስብሰባውን በመልቀቅ ይሰናበታል። ይኸው የቦርድ ውሳኔ በPress release በወቅቱ ለሚመለከታቸው ሁሉ ተሰራጭቷል።

የPress releaseን በዚህ ፎረም ላይ ሳሰራጭ የማንንም አስተያየት አላየሁም። ከዚያ በኋላ ለረጅም ጊዜ እዚህ ፎረም ውስጥ ግንኙነቴ እንዲቋረጥ በመደረጉ ተወይታችሁበት እንደሁ አላውቅም። delet ካላደረጋችሁት በጃኑዋሪ/ፌብሯሪ 2008 (EFJA) yahoo group forum ላይ የተሰራጨውን የኢሜል መልእክት መመልከት ይቻላል። የPress releaseን ላልተመለከታችሁ ግን እነሆ አባሪ ላይ ማግኘት ይቻላል።

እግረመንገዱንም ዳዊት ከበደ *“እንዴት የነጻው ፕሬስ ጅምር ወደ ድርጅት ተቀለበሰ?”* ሲል ላነሳው ጥያቄ በቂ ምላሽ ይሰጣል የሚል እምነት አለኝ።

የቦርዱ ቀጣይ እርምጃ የነበረው ከአቶ ከፋለ ጋር ስለጉዳዩ መወያየት ነበር። ከቦርድ አባላት የቀረበለት ጥያቄና ወቀሳ እንደ ሊቀመንበር ሃላፊነትህ አንድ የድርጅቱ የቦርድ አባል የድርጅቱን ሰነድ ዘርፎ ለሌላ የግል ጥቅሙ ሲያውል እያወቅክ እንዴት በይሁንታ አለፍከው? በዚህም የነጻው ፕሬስ ሃላፊነትህን አልተወጣህም የሚል ነበር። በሚያሳዝን ሁኔታ አንድም አሳማኝ ምክንያት አልነበረውም። ስለዚህ በራሱ ጥያቄ ቦርዱ ለአንድ ቀን እድሜ ሶስት አማራጮችን ሰጥቶት አሰናበተው። የውሳኔ አማራጮቹም 1. በቂና አሳማኝ ምክንያቱን እንዲያቀርብ 2. ምክንያቱ በቂ ካልሆነ ቦርዱ የሚወስንበትን ከሊቀመንበርነት ቦታው ተነስቶ በተራ የቦርድ አባልነት እንዲያገለግል 3. በፍቃደኝነት እራሱን ከቦርድ እንዲያገል የሚል ነበር። በነጋታው በተደረገው ስብሰባ ላይ አቶ ከፋለ ለቦርዱ የሚሰጠው አስተማማኝ ምክንያት ስላልነበረው እራሱን ከቦርድ ሊቀመንበርነቱም ሆነ አባልነቱ አሰናበተ።

ከዚህ በኋላ ነበር የነጋሪት ፕሮጀክት ውድቀት በከፈተኛ ደረጃ አሽቆልቁሎ በወራት እድሜ ውስጥ ያበቃለት። ይህ ነበር ነጻና አማራጭ የመገናኛ ብዙሃን የተባለውና በራስ ወዳዶች ከመንገድ ላይ ተጠልፎ ደብዛው እንዲጠፋ የተደረገው። በሁኔታው ያዘኑትና በብልሹ አሰራሩ ያልተደሰቱት በቅድሚያ Press Now ዳይሬክተር Wilco de Jong በኋላም ከቦርድ አባላት መካከል ዶ/ር ወንድሙ መኮንንና አቶ አበራ ለማ ፕሮጀክቱንና ቦደርዱን ለቀው ወጡ። የተጓደለውን ቦርድ ለመጨረሻ ጊዜ የተሰናበትነው እኔና ለስራው በዝግጅት ላይ የነበርነው ጋዜጠኞችና በጎ አድራጊዎች ነበርን።

ከዚህ በኋላ ለጊዜውም ቢሆን የተሳካላቸውና ያደረጉት ሙከራ ቢኖር እኔን (EFJA) yahoo group forum ግንኙነት እንዳላደርግ ከአንድ አመት በላይ ብሎክ ማድረግ ነበር። ይንንም በአንድ ቴሌ ኮንፍረንስ ላይ ገልጬ በስህተት ወይም በቴክኒክ ችግር ሳብያ ተደርጎ ሊሆን ይችላል፤ አይተን እናስተካክላለን ነበር የተባለው። ግን አልተደረገም። ማወቅ ደግ ነውና ከአድሚኖቹ መካከል ለግርማ እንድሪያስ ደውዬለት እንደገና መዘገበኝ። ይህን ግሩፕ አድሚን የሚያደርጉት ዳዊት፣ ክንፋና ግርማ ናቸው። ሌላ አራተኛ፣ አምስተኛ ሰው እንዳለ አላውቅም። ታድያ ማን ነው ተጠያቂው?

የሚገርመኝ ሰሞኑንም ይኸው ሁኔታ በድጋሚ ተከሰተ። ዳዊት “ይህ ሁኔታ በአንድ ግለሰብ ላይ በውሳኔ ከተደረገው ውጭ፤ እንዲህ አይነት ተግባር አይፈጸምም” ሲል የሰጠውን ማስተባብያ አንብቤአለሁ። በእኔ ላይ ከአንዴም ሁለቴ ተፈጽሟል!! አሁን ሰሞኑን የምትለዋወጡትና የሚንከባለለው ሃሳብ በቀጥታ እኔን የሚመለከት እየሆነ የሚደርሰኝ በስማ ስማ ነበር። “ወልደማሪያም” ከፎርሙ ሰሜን ሲደልዝ ለግርማ እንድሪያ አቤት ብዬ እንደገና መመዝገብ ነበረብኝ? *“ወያኔ ዌብሳይታችንን ብሎክ አደረገ፤ ሃሳብን በነጻነት መብታችንን ተጋፋ”* የምንል የነጻው ፕሬስ ሰደተኛ አርበኞች እንዴት የራሳችንን መብት ማክበር ይሳነናል?

በዚህ አካሄድማ እዚህ ውሰጥ እነማን እንዳለንም አናውቅም። በእርግጥስ በስደት ላይ ካሉት በርካታ የሚባሉ ጋዜጠኞች በምን ምክንያት የዚህ ፎረም አባል አልሆኑም? መመዘኛ ይኖረው ይሆን? ወይስ የጋዜጠኝነት ስያሜ ሰጪና ነሺም አለ? ጉዳዩ በርካታ ሰበዞችን ሊመዝ ይችላል። በርካታ ጥያቄዎችም ሊነሱ ይችላሉ።

**<u>ጥቂት ስለገንዘብ ጉዳይ፦</u>** ከላይ እንደጠቀስኩላችሁ ለነጋሪት ፕሮጀክት የ111.000 ኤሮ አርዳታ በቃልና ጽሁፍ የስምምነት ውል ተደርጎልን ነበር። በተጨማሪም በእንጥልጥል ቀረ እንጂ ለሶስት ተከታታይ አመታት በየአመቱ የ65.000 ኤሮ ተሰፋ ነበር። ከ111.000 ኤሮ የስምምነት ውል ውስጥ ወደ FIME የባንክ አካውንት የተላለፈው አንደኛው ድርጅት ለመርዳት ከተስማማው የ35.000 ኤሮ ውስጥ የ20.000 ኤሮ ቅድሚያ ክፍያ በማድረጉ ነበር።

በFIME የባንክ አካውንት የተላለፈው 20.000 ኤሮ በተመለከተ ምንም ስራ ሳይሰራበት 17.000 ኤሮ ለበጎ አድራጊው ድርጅት ተመላሽ እንደተደረገ በተጓደለ አባላት ብቻውን የቀረውን የቦርድ ሪፖርት አንብቤአለሁ።

**<u>ኢሳት በአምስተርዳም ስለመቋቋም፦</u>** ኢሳት በአምስተርዳም ስለመቋቋሙ ያወቅኩት እንደማንኛውም ሰው በስተኋላ ነው። ቀደም ሲል ቅንጅት ብለው ሲንቀሳቀሱ ከነበሩት ግለሰቦችም ሆነ አሁን አቶ ከፋለ “ከኢሳት ለቅቄአለሁ” ብሎ ባሰራጨው ደብዳቤው ውስጥ እንደገለጸው ስለ ኢሳት ምስረታ ከዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ጋር በተደረጉ ውይይቶች ላይም አልተገኘሁም። የአቶ ከፋለንም ሆነ የክንፉን ተሳትፎ ስመረምር ኢሳት በኢትዮ-ቲቪ እና በነጋሪት ፕሮጀክት ህልውና ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለኝም።

ኢትዮ-ቲቪን በኋላም በነጋሪት ሬድዮና ቴሌቭዥን ፕሮጅክት የታስክ ፎርስ፣ ቦርድና በስራ ገበታው ላይ ለፕሮጀክቱ መሳካት ጊዜአቸውን፤ ጉልበታቸውን እና ገንዘባቸውን በቅንነት በማገልገል መስዋዕት ባደረጉ ግለሰቦች ላይ ተሸርቦ ለተቋቋመ ድርጅት በሽምግልናም ሆነ በመልእክተኝነት በሚሰጥርም ሆነ ባደባባይ ያነጋገሩኝን ግለሰቦች በሙሉ በምንም መልኩ አብሬአቸው ለመሰለፍ እንደማልፈቅድ አረጋግጬላቸዋለሁ።

*“ኢሳት እንዴት በግንቦት ሰባት መዳፍ ላይ ወደቀ?”* ለሚለው ጥያቄ፤ በስም ለመጠቀም ካልተፈለገ በስተቀር ይህ ድርጅት ቀድሞውንም በምንም ሚዛን የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች ባለቤትነትም ሆነ ተጠያቂነት ያለበት ባለመሆኑ ለክርክር አያበቃንም። ይህንኑ አቶ ከፋለ ማሞ በኢሳት አለቃው ላይ ክስ በሰነዘረበት ደበዳቤ ላይ በራሱ ጽሁፍ ያረጋግጣል። *“ኢሳት የማን ነው?”* ለሚለው ጥያቄ በኔ በኩል የሁል ጊዜዩ መልሴ አንድ ቀን “ባለቤቱ እኔ ነኝ” እስኪለን “የህዝብ ነው” የሚሉትን እየሰማን መጪውን ማየት ነው። ጊዜ የማይፈታው ምን አለ ብላችሁ ነው?

ሃቁ ይኸው ነው!

ኢትዮጵያን የእውነት አምላክ ይጠብቃት!

ክብረት መኮንን፤ አምስተርዳም